የሰ/መ/ቁ. 59953

ሰኔ 02 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ዓለምነሽ አበበ-

**ተጠሪ** ፡- አቶ ተስፋዬ ገሠሠ-

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ፍቺን ተከትሎ የተነሳውን የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-ከተጠሪ ጋር ከ1970 ዓ/ም ጀምሮ አብረው እንደባልና ሚስት ከኖሩ በኂላ ታህሳስ 25 ቀን 1977 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የፈጸሙት ጋብቻ ከሚያዚያ 18 ቀን 1994 ዓ/ም በፍቺ መፍረሱን፣በጋራ የሠሩትን ቤት ቁጥር 398ሀ1 የሆነን ቤት እንዲከፋፈሉ አመልካች ተጠሪን ጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ ከ1989 ዓ/ም እስከ 1992 ዓ/ም በወር ብር ከ800.00(ስምንት መቶ ብር)፣ከ1992 እስከ 1997 ዓ/ም ብር 900.00፣ከ1997 ዓ/ም ጀምሮ በአመት ብር 20,000.00 ተጠሪ ቤቱን እያከራዩ ገቢውን ለአመልካች ሊከፍሏቸው ያልቻሉ መሆኑን ገልፀው በቤቱ ኪራይ የሚገኘውን ገቢ እንዲያካፍሏቸውና ቤቱን በስምምነት ሽጠው ለመከፋፈል ፈቃደኛ ካልሆኑ በሐራጅ ተሽጦ እንዲከፋፈሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በማንሳት የተከራከሩት ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ነው በሚል ነው፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበውን መቃወሚያ በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር ጉዳዩ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት የማይገባ ነው በማለትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 እና 244(2(ለ)) ድንጋጌዎችን በዋቢነት በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ ሙሉ ጸንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በአሜሪካን አገር የሚገኝ ፍርድ ቤት በግልፅ ዳኝነት የሰጠበት ስለሆነ ዳግመኛ ዳኝነት መጠየቅ አይቻልም በማለት መዝገቡ የተዘጋው የተሰጠው ዳኝነት ኢትዮጵያ ያላችሁንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ያጠቃልላል የማይል ሁኖ እያለ በተሳሳት ትርጉም ፍርድ አርፎበታል መባሉ

ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርመሮም አመልካች በኢትዮጵያ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት አቤቱታ ዳግመኛ የተጠየቀ ዳኝነት ነው በማለት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም የአሜሪካን አገር የሚገኘው ፍርድ ቤት በሁሉም የጋብቻ ውጤቶች ላይ ውሳኔ ያሳረፈ መሆኑን ጠቅሰው በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግብብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የፍቺ ውሳኔም ሆነ የንብረት ውሳኔ የተሰጠው በአሜሪካ ሀገር ሜሪላንድ እስቴት ሞንትጎመሪ ካውንት ፍርድ ቤት በቤተሰብ ሕግ ቁጥር 21746 በሆነ በ25/08/94 ገቢ የሆነበት ማስረጃ መኖሩን፣ይህ ማስረጃ ግራ ቀኙ ንብረታቸውን በጋራ እርካታ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንደተከፋፈሉና በማንኛውም ወገን የንብረት ባለመብትነት ይገባኛል ጥያቄ ለዳኝነት እንዳይቀርብ የታዘዘ ስለመሆኑ እንደሚያሳይ፣ከዚህ በተጨማሪ ባለጉዳዮቹ የገንዘብ ነክ ፍርድን በጋራ በራሳቸው ፈቃድ እንደተው መታዘዙን እንደሚገልፅ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ መግለፁን፣በውጪ አገር የተሰጠ ውሳኔም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ የቀረበ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማረጋገጡን ነው፡፡እንግዲህ የስር ፍርድ ቤት የውጪ አገር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውንም ሆነ የንብረትና የገንዘብ ክርክራቸውን በአሜሪካን አገር ፍርድ ቤት በስምምነት ቀርበው ውሳኔ ያሰጡ መሆኑን በመገንዘብ የአመልካችን ጥያቄ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱን  የውሳኔው ግልባጭ የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንድ የመጨሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5  ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት የገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣በትእዛዝ፣ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች አሻሽለው በ08/03/2001 ዓ.ም ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ጋብቻው መፍረሱን ገልጸው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለና በጋራ የሠሩትን ቤት ቁጥር 398ሀ1 የሆነን ቤትና በቤቱ የተገኙትን ፍሬዎች እንዲከፋፈሉ አመልካች ተጠሪን ጠይቀው ተጠሪ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአሜሪካን አገር ተሰጠ የተባለው ውሳኔ ግራ ቀኙ ንብረታቸውን በጋራ እርካታ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ እንደተከፋፈሉና በማንኛውም ወገን የንብረት ባለመብትነት ይገባኛል ጥያቄ ለዳኝነት እንዳይቀርብ የታዘዘ ስለመሆኑ እንደሚያሳይ፣ከዚህ በተጨማሪ ባለጉዳዮቹ የገንዘብ ነክ ፍርድን በጋራ በራሳቸው ፈቃድ እንዲተው መታዘዙን እንደሚገልፅ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ይሁን እንጂ የውጪ አገሩ ፍርድ ኢትዮጵያ ውሥጥ ያለውን ንብረት እንደተከፋፈሉ ወይም በራሳቸው ፈቃድ እንደተው የሚያሳይ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶበታል የሚባለው በመጀመሪያው ክርክር ላይ በአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ ሲሆን ነው፡፡በመሆኑም አንድ ጉዳይ በፍርድ አልቋል የሚለው ተቃውሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የሚኖረው በሕጉ የተመለከቱት መመዘኛዎች መሟላታቸው በቅድሚያ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግን ግራ ቀኙ በጋብቻ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ንብረት በተመለከተ በውጪ አገር ባለ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ስለመሆኑና ይህም ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ከቁጥር 456 እስከ 461 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሚያሳዩት መልኩ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነትን ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ በግልፅ መሟላቱ ሳይረጋገጥ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የአመልካችን ዳኝነት ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118249 መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92036 ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ፍሬውን ለመካፈል ያቀረቡት አቤቱታ ዳግመኛ የተጠየቀ ዳኝነት አይደለም ብለናል፡፡

3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 118249 የቀረበውን ክርክር ቀጥሎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1)መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡